የወ/መ/ቁጥር 165525

የልደታ ምድብ 5 ኛ ወንጀል ችሎት

ሐምሌ 20 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፣ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፣ 1 ኛ አቶ ምትኩ አወል አብዛ - ተቋረጠ

2 ኛ አቶ ሸምሱ በርጋ አብዛ - ቀረበ

መዝገቡ ተመርምሮ በ 2 ኛ ተከሳሽ ላይ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ ጥር 12 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የወንጀል ክስ አቤቱታ ተከሳሾች በ 1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1)(ሀ) እና 556(2)(ሀ) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በሰው ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ ታህሳስ 28 ቀን 2001 ዓ.ም በግምት ከቀኑ 5፡00 ሰዓት ሲሆን በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/05 ክልል ውስጥ ልዩ ቦታው ማርስ ካፌ ዝቅ ብሎ ሰባ ሰባት መጋዘን ጠጅ ቤት አካባቢ የገል ተበዳይ አቶ ተመስገን መስፍንን አንደኛ ተከሳሽ በእጁ የለበሰውን ሽርጥ አንቆ ይዞ እንዳይከላከል ሲያደርግ፤ ሁለተኛ ተከሳሽ ደግሞ ድንጋይ ጨብጦ በቦክስ ማጅራቱንና ጎኑ ላይ በመምታት ለጊዜው ሕሊናውን እንዲስት በማድረጋቸው በዋና ወንጀል አድራጊነት በፈፀሙት ቀላል የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ተከሰዋል በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሾች ደርሷቸውና ተነቦላቸው ከተረዱት በኋላ ክሱን ሳይቃወሙ፤ ድርጊቱን አልፈፀምንም፤ ጥፋተኞች አይደለንም ብለው ክደው በመከራከራቸው ዐ/ሕግ በሁለተኛ ተከሳሽ ላይ የግል ተበዳይን ጨምሮ ሦስት ምስክሮችን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የተሰጠ የግል ተበዳይን የጉዳት ሁኔታ የሚገልፅ የህክምና ማስረጃም አቅርቦ አሰምቷል። በዚህም መሰረት በግል ተበዳይ ላይ በክሱ ላይ በተመለከተው ሁኔታ ጉዳት የደረሰበት መሆኑና ይህን ጉዳትም ሁለተኛ ተከሳሽ ከሌላ ግለሰብ ጋር በመሆን ጉዳቱን ያደረሰ መሆኑን በቦታው የነበሩት ምስክሮች ጭምር በማስረዳታቸው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(2)(ሀ) ስር እንዲከላከል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዟል። አንደኛ ተከሳሽን በተመለከተ ግን ክርክሩ ዘግይቶ በመጀመሩና ዐ/ሕግ በዚሁ ተከሳሽ ላይ ማስረጃዎቹን ለማቅረብ ባለመቻሉ ክሱ በእሱ ላይ የተቋረጠ መሆኑን መዝገቡ ያስረዳል።

ሁለተኛ ተከሳሽ እከላከላለሁ ብሎ ሁለት ምስክሮችን በማቅረብ ያሰማ ሲሆን በመከላከያ ጭብጥነትም ያስመዝገበው በወቅቱ ቦታው ላይ ምንም አይነት የወንጀል ድርጊት አልፈፀምኩም በመከላከያ ምስክሮቼ አስረዳለሁ፤ ምክንያቱም አንደኛው ምስክሬ ባለሱቅና በቦታው ስለነበር ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ከእኛ ጋር አብሮ የሚሰራ ልጅ ስለሆነ ነው። በወቅቱ የግል ተበዳይ መሬት ላይ ወድቆ ክብሪት ሲለኩሱለት ነው እኔ የመጣሁት፤ እኔ በጊዜው ተበዳይ

ምን ሆኖ ነው ስል በሽታ አለበት፤ አዙሪት በሽታ አለበት ብለው ሲለኩሱለት ነው ከስራ ቦታ ውጥቼ ይህን ሁኔታ ያየሁት በማለት አስመዝግቦ በዚሁ መሰረት ሁለቱ የመከላከያ ምስክሮች ቀርበው በእምነታቸው መሰረት መኃላ ፈፅመው የመሰከሩ ሲሆን ቃላቸውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል።

ፍ/ቤቱም ሁለተኛ ተከሳሽ ባቀረበው የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበበትን ክስና ማስረጃ አስተባብሏል ወይ የሚለውን ነጥብ የመረመረ ሲሆን የሁለተኛ ተከሳሽ የመከላከያ ምስክሮችን ቃል ፍ/ቤቱ ሲመረምረው አንደኛው ምስክር በወቅቱ ጠጅ ቤት ውስጥ ሥራ ላይ ተሰማርቶ የነበረ መሆኑን፤ በኋላ ደግሞ ተበዳይ ተመታ ተብሎ ሲወጣ ተበዳይን መሬት ላይ ወድቆ እንዳገኘውት ማን መታው በማለት ሲጠይቅም አንደኛው ተከሳሽ አቶ ምትኩ አወል ነው በማለት ሰዎች ነግረውኛል ከማለት ውጭ እርግጠኛ በሆነ መልኩ የግል ተበዳይን ማን እንደመታው ያላስረዳ ሲሆን፤ ይህ ደግሞ የዐ/ሕግ ሦስት ምስክሮች ሁለተኛ ተከሳሽ በወቅቱ ድንጋይ በእጁ ጨብጦ ይዞ ተበዳይን ሲመታ በአይናቸው ያዩትን የሚያስተባብል ሆኖ አልተገኘም። ሁለተኛው የመከላከያ ምስክርም ቢሆን በወቅቱ ሱቅ ውስጥ ስራ ላይ የነበረ መሆኑን ገልፆ የግል ተበዳይን አንደኛ ተከሳሽ ሲመታው አይቻለሁ በማለት የመሰከረ ቢሆንም ሁለተኛው ተከሳሽ የግል ተበዳዩን አልመታውም በማለት ለማስረዳት አልቻለም። በመሆኑም ሁለተኛ ተከሳሽ ባቀረበው የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበበትን ክስና ማስረጃ ለማስተባበል ስላልቻለ በተከሰሰበት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(2)(ሀ) ስር ጥፋተኛ ነው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

ዐ/ሕግ፡ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84(1)(መ) መሰረት ድርጊቱ በጋራ የተፈፀመ

ስለሆነ ፍ/ቤቱ ቅጣቱን አክበዶ እንዲወሰን በማለት አመለከተ፡

ሁለተኛ ተከሳሽ፡ ዕድሜዬ 21 ዓመት ነው፤ ትዳርና ልጅ የለኝም፤ የምኖረው ብቻየን ሲሆን፤ በአስተናጋጅነት ተቀጥሬ በወር ብር 300.00(ሦስት መቶ ብር አገኛለሁ፤ ከግል ተበዳይ ጋርም ታርቀን በሰላም እየኖርን ነው ብሎ የታረቁ መሆኑን የሚገልፅ በግል ተበዳይ የተፃፈ ማመልከቻ ያቀረበ ሲሆን የግል ተበዳይም ቀርቦ ይህንኑ አረጋግጧል።

ፍ/ቤቱም መዝገቡን መርምሮ የሚከተለው የቅጣት ውሳኔ ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ሊያሳካ እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ

ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወስነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ክብደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ሁለተኛ ተከሳሽ አሁን ጥፋተኛ የተባለበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(2)(ሀ) ደረጃ የወጣለት ወንጀል በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል አንድ እና አባሪ 3 መሰረት የተመለከተው ደረጃ 2 ሲሆን ተጓዳኝ መነሻ እርከኑም 5 ነው። ስለሆነም የዚህ እርከን መነሻ ፈቃደ ስልጣን/range/ ከስድስት ወር እስከ ዘጠኝ ወር ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም ፍ/ቤቱ ቅጣቱን የሚወስነው የተከሳሽን የትምህርት ደረጃና ዕድሜ ከግምት ውስጥ በማስገባት መነሻ ቅጣቱ ሰባት ወር ቀላል እስራት እንዲሆን ነው ያደረገው።

በዚህም መሰረት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት አመዛዝኖ ቅጣት ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84(1) (መ) መሰረት አንድ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ያቀረበ ስለሆነ እርከኑ ወደ 6 ከፍ ተደርጓል።

ተከሳሽ በበኩሉ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82 እና 86 መሰረት የቅጣት ማቅለያ በማስረጃ አስደግፎ ያላቀረበ በመሆኑ የቅጣት እርከኑ ዝቅ ሳይል አንዳለ እርከን 5 ሆኗል።

በዚህም መሰረት በማክበጃው ከፍ ያለው የእርከን 6 ፍቅደ ስልጣን ከስምንት ወር እስከ አንድ ዓመት በመሆኑ ተከሳሽን ያርማል፤ ወደፊትም ያስተምራል ብሎ ፍ/ቤቱ ባመነበት በዘጠኝ ወር ቀላል እስራት እንዲቀጣ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. ሁለተኛ ተከሳሽና የግል ተበዳይ ጉዳያቸውን በእርቅ ጨርሰው ተስማምተው
በሰላም እየኖሩ ስለሆነ፤ ሁለተኛ ተከሳሽ ከአሁን በፊት በሌላ የወንጀል
ድርጊት የማይታወቅ ስለሆነ፤ በግል ተበዳይ ላይ የደረሰው ጉዳት ቀላል
በመሆኑና በአሁኑ ወቅት በደህና ሁኔታ ላይ የሚገኝ ስለሆነ፤ የእስራት ቅጣቱ
ከሚፈፀም ይልቅ ለተከሳሹ አንድ ዕኑ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶ የወደፊት አመልና
ፀባዩን ማየቱ በቂ ስለሆነ የእስራት ቅጣቱ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 192
መሰረት በሁለት ዓመት ገደብ ታግዷል።

2 ኛ. ሁለተኛ ተከሳሽ የገደብ ጊዜው እስኪጠናቀቅ ድረስ ለዋስትና ያስያዘው
ገንዘብ ለመልካም ፀባይ አመራር ዋስትና ይሆን ዘንድ በወንጀል ሕግ አንቀፅ
197(2) መሰረት ባለበት እንዲቆይ ታዟል።

3 ኛ. ሁለተኛ ተከሳሽ ለመንግስት የፅህፈት ወጪ ብር 25.00(ሃያ አምስት ብር)

ይክፍል። ሲከፍልም ይለቀቅ።

4 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

5 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።